የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ

(ኢዜማ)

የወጣቶች ፖሊሲ

ሚያዚያ 2012 ዓ.ም

ማውጫ

1. የፖሊሲው መነሻመልዕክት 4

2. የሚያጸደቀው አካል፣ የሚተገበርበት ቀን እና የሚሻሻልበት ዘመን 4

3. መግቢያ 4

4. ዳራ 4

5. ዓላማ 6

6. መርህ 6

7. የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎች 7

7.1. የትምህርት ሥርዓትን ተደራሽ እና ጥራት ያለው ማድረግ 7

7.1.1. የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት 7

7.1.2 የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ 7

7.1.3. በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት አሰጣጥ 8

7.1.4. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወጣቶች 8

7.1.5. የወጣት ክበባት እና ህብረቶች 8

7.2. ጤናማ ወጣትን መፍጠር 9

7.2.1. ወጣቶች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማስቻል 9

7.2.2. ወጣቶች በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በስፋት እንዲሳተፉ ማስቻል 9

7.2.3. የሥነ-ልቦና አገልግሎትን በስፋት ተደራሽ ማድረግ 9

7.2.4. ጤናማ የሥነ-ተዋልዶ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል 10

7.3. ወጣቶች ተጋላጭ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች በመከላከል እና በማስወገድ መልካም ወጣቶችን መፍጠር 10

7.3.1. ሴት ወጣቶችን ተጋላጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ማስወገድ 11

7.3.2. በወንጀል ድርጊት ተሳትፈው የሚገኙ ታራሚ ወጣቶች 11

7.3.3. አካል ጉዳተኛ ወጣቶች- መላኩ የፂ ጓደኛ 11

7.3.4. በተለያዩ ሱሶች የተጠቁ ወጣቶች 11

7.3.5. በአርብቶ አደር እና በገጠር አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች 12

7.3.6. ለስደት ተጋላጭ የሆኑ እና ከስደት ተመላሽ ወጣቶች 12

7.4. የስፖርት ፣ መዝናኛ እና ባህል እንቅስቃሴዎች በማሳደግ ወጣቱን ተጠቃሚ ማድረግ 12

7.4.1. ስፖርት 12

7.4.2. መዝናኛ 13

7.4.3. ባህል 13

7.5. የወጣቱን የአገር ፍቅር ስሜት እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማሳደግ 14
7.5.1. የወጣቱን የበጎ ፍቃድ አገልጎልት ማጎልበት 14
7.5.2. የወጣቱን አገር ፍቅር ስሜት የማሳደግ ሥራዎችን መስራት 14
7.6. ወጣቶች ትርጉም ያለው ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል 15
7.7. ወጣቶች ለሰብዓዊ መብቶች እና ለዴሞክራሲያዊ ማህበረብ ግንባታ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ማስቻል 16
7.8. የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ 16
7.8.1. ወጣቶች በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል 16
7.8.2. ወጣቶች በመረጃና ግንኙነት ቴክኖሊጂ (Information and communication Technology) ዘርፍ በስፋት እና በጥራት እንዲሳተፉ ማስቻል 17
7.8.3. የወጣቱ ከግብርናው ዘርፍ ያለውን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ 19
7. ኃላፊነት እና ተግባር 20
7.1. መንግስት 20
7.2. ወጣቶች 20
7.3. መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት (አለም አቀፍ እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች) 20
7.4. ቤተሰብ 21
7.5. የሃይማኖት ተቋማት 21
8. አባሪ 21

1. የፖሊሲው መነሻመልዕክት

በፓርቲው መሪ/ ሊቀመንበር ወይም የፖሊሲና ጥናት ዋና ተጠሪ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያስብ የፖሊሲውን መልዕክት ሊፃፍ ይችላል።

2. የሚያጸደቀው አካል፣ የሚተገበርበት ቀን እና የሚሻሻልበት ዘመን

ይህን ፖሊሲ የሚጸድቀው የፓርቲው ከፍተኛ አካል/ሥራ አስፈጻሚ ወይም የፓርቲው መሪ ክንፍ ሲሆን ወደ ተግባር የሚገባው ከ ..... ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፤ ለመሻሻል ወይም እንደ አዲስ ለመቀየር የሚታሰበው ---------- ጊዜ ይሆናል።

3. መግቢያ

የወጣትነት የዕድሜ ዘመን በባህሪው ስሜታዊነት እና ተነሳሽነት የሚስተዋልበት የክህሎት እና የወረት ማከማቻያ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን እጅግ በጥንቃቄ ሊቃኝ እና ሊደገፍ ይገባል፡፡ የአገራችን እና የሌሎች አገራት ታሪካዊ ልምዶች እንደሚያሳዩት ለአንድ አገር ውድቀት እና መነሳት የወጣቱ ሚና ከየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል በላይ ወሳኝነት እንዳለው ነው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ካላት የህዝብ ቁጥር ሰፊውን ድርሻ የሚይዘው የወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ሰፊ የማህበረሰብ ክፍል አግባብነት ባለው፣ ዘመኑን የዋጀ የአስተዳደር ማዕቀፍ ባለመስተናገዱ አማካኝነት ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም። ይባስ ብሎም ለአገር ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ለኢኮኖሚ ዕድገት ማነቆ ሲሆን በመስተዋል ላይ ይገኛል። ወጣቶች የአገራችን ኢትዮጵያ ማዕከል እንደመሆናቸው በአገር አቀፍ እንዲሁም በሌሎች የመንግስትና የግል ዘርፍ እርከኖች ትርጉም ባለው መልኩ ሊሳተፉ ይገባል። ይህን ማድረግ ወጣቶችን ብቻ ሳይሆን የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የማድረግ ዕድሉ ሰፊ ነው። እነዚህን ምክንያቶች ማዕከል በማድረግ ይህ የኢዜማ የወጣቶች ፖሊሲ ሰነድ ወጣቱ ሃላፊነት በተሞላበት መንፈስ የአገር አንድነት እና ሉአላዊነትን እንዲያስከበር፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ከዚያም ባሻገር ከራሱ አልፎ ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መብት መከበር እንዲቆም ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን እንዲያፋጥን ፣ ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት መሪውን ድርሻ እንዲወስድ ታቅዶ የተቃኘ ሰነድ ነው፡፡ የፖሊሲ ሰነዱ የኢትዮጵያ ወጣት ዜጎች ያሉበትን ሁኔታ እንዲሁም ወደ ፊት ሊገጥሟቸው የሚችሉትን አገራዊ እና አለማቀፋዊ መሰናክሎችን እና ዕድሎችን በጥልቀት በመመርመር ለወጣቶች ማህበረሰባዊ ፍትህን በማስፈን ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ወጣቶች ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ዕድገት አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ለማድረግታስቦ የተቀረፀ ፖሊስ ነው።

4. ዳራ

ወጣቶች ለአንድ አገር ቁልፍ የሃብት ምንጮች መሆናቸው ፤ እንዲሁም አስፈላጊው ድጋፍ ከተደረገላቸው ለአገር ልማትናዕድገት፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንዲሁም ማህበራዊ ፍትህ መረጋገጥትልቅ ሚና እንደሚጫወቱ ይታመናል። የኢትዮጵያ ወጣቶችም እንዲሁ ለአገራቸው ትልቅ ሚና መጫወት የሚችሉ ወረቶች ናቸው። በተለምዶ ወጣቶች የሚባሉት አስገዳጅ ከሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (Compulsary Primary education) ማብቂያ አንስቶ ወደ ሥራ አለም የሚቀላቀሉበት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ናቸው። ወጣት የሚለው የዕድሜ ክልል በተለያዩ አለም አቀፍ ሰነዶች ላይ የተለያየ ትርጓሜ ተሰቶት የሚገኝ ሲሆን ወጣት የሚለው ቃል ግን ሰዎች ከቤተሰብ ጥገኝነት ወደ ራስ መቻል የሚገባበትን የሽግግር ጊዜ የሚያመላክት እንደሆነ ይጠቀሳል።

በዚህም መሰረት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸኃፊ ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት(UNICEF/WHO/ UNFPA) እና አለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት (ILO) ወጣት የሚለውን የዕድሜ ክልል ከ15-24 ዓመት መካከል ባለው ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ሲቆጥር፤ UN Habitat ደግሞ ከ15 እስከ 32 ዓመት ዕድሜን የወጣትነት ዕድሜ ወሰን ሲያደርግ የአፍሪካ የወጣቶች ቻርተር ደግሞ የዕድሜ ገደቡን ከ15 እስከ 35 አድርጎታል። ይህን ቻርተር ኢትዮጵያ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እ.ኤ.አ በ2014 ዓ.ም ያፀደቀች ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ. ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 9(4) መሰረት ይህ የወጣቶች ቻርተር የኢትዮጵያ ሕግ አካል ተደርጎ ስለሚቆጠር ኢትዮጵያ ውስጥ የወጣትነት ዕድሜ ክልል ከ15 ዓመት እስከ 35 ዓመት ነው ማለት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቶች ሰፊ የሆነ የህዝብ ቁጥርን የሚሸፍኑ ሲሆን ከ10-29 ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች ከህዝብ ቁጥር 42% እንዲሁም ከ10-24 ዕድሜ ክልል ደግሞ ያሉት 33% እንደሆኑ መረጃዎች ያመላክታሉ። እንዲህ ባለው ሁኔታ ወጣቱን ያላማከሉ ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ ሳይታለም የተፈታ ነው። ወጣቱ አሳታፊ፣ ምቹ እና አስቻይ ሁኔታዎች ከተፈጠሩለት ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕድገት የጀርባ አጥንት በመሆን የላቀ አስተዋጽዖ ማድረግ የሚችል ሲሆን አሳታፊ፣ ምቹ እና አስቻይ ሁኔታዎች ካልተመቻቹለት ደግሞ በተቃራው አገሪቱን ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ውስጥ የሚከት የጥፋት እና የአጥፊዎች መሳሪያ ይሆናል ። በአሁኑ ወቅት በአገራችን ከፍተኛ የሆነ ቁጥር ያለው ወጣት አሳታፊ፣ ምቹ፣ አስቻይ እና አበረታች የሆኑ የህግ፣ የአሰራርና ተቋማዊ ማዕቀፎች ባለመሟላታቸው ምክንያት ወጣቱ በዜግነቱ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያገኝ ብሎምለአገሩ ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም እንዳይሰጥ አድርጎታል። ለዚህ የተለያዩ እንደ ደካማ የትምህርት ሥርዓት፣ ትርጉም የለሽ ተሳትፎ እና አድሎዓዊ አሰራሮች ያሉ ተጠቃሽ ገፊ ምክንያቶች ሲኖሩ የአገራችን ወጣቶች በአሁኑ ወቅት በሥራ አጥነት ፣በስደት፣ በተለያዩ ሱሶች፣ በአክራሪነት፣ በዓላማ እና ተስፋ ማጣት የተጠቁ ሁነው ይገኛሉ። በከተማም በገጠርም የሚገኙ መጠነ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ለአገራቸው ያላቸው ፍቅር ተመናምኖ፣ በሃገራቸው የመኖር ተስፋቸው ተሟጦ፣ ስደትን እንደቀዳሚ አማራጭ ቆጥረው ከአገር በመሰደድ አልያም በከፋ ሁኔታ ውስጥ በአገር ውስጥ ይገኛሉ። በአገር ውስጥም የሚገኘው ወጣት በአገሩ ጉዳይ የበይ ተመልካች ተደርጎ በአንድ በኩል በሱስ በሌላ በኩል በአክራሪነት ተጠምዶ ከፍተኛ በሆነ ብክነት ውስጥ ይገኛል።

እነዚህን ዘርፈ ብዙ የሆኑ የአገራችንን ወጣቶች አሉታዊ ዑደት ያላቸው ችግሮች ውስጥ የከተቱ ተግዳሮቶችን በመመርመር፣ ለወጣቱ ችግሮች መንስኤ የሆኑ ሁኔታዎችን በመተንተን የወጣቶችን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት የወጣቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማዕከል ያደረገ እና የወጣቶችን የሃብት ምንጭነት ሊያረጋግጥ የሚችል የፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ይህ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ የወጣቶች ፖሊስ ተሰናድቷል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ(ኢዜማ) በአገራችን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የወጣቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ አለመኖሩን በማመን፣ ደካማ ከሆኑ የትምህርት፣ የጤና፣ የመሬት እና ሌሎች የአስተዳደር ሥርዓቶች የመነጩ የሥራ አጥነት/የከተማ እና የገጠር/ ፣ የስደት፣ የሱስ ፣ የተስፋ ማጣት፣ የበሽታዎች /HIV/AIDS እና አባላዘር በሽታዎች/ ተጠቂነት መፍትሄ ለመስጠት እንዲሁም እነዚህ ችግሮች በዘላቂነት እንዲፈቱ ከዚያም ባለፈ ወጣቱ ኢትዮጵያን ከፍ ወዳለ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ የልህቀት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ታላቅ ሃብት መሆኑን በማመን ይህን ዕውን ማድረግ የሚችል የፖሊሲ ማዕቀፍ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን ፖሊሲ ሊያወጣ ችሏል። ፓርቲው በፕሮግራሙ እንዲሁም በብሔራዊና በምርጫ ወረዳ ደረጃ ባሉ አደረጃጀቶች ወጣቱን የሚመለከቱ ክፍሎች በማካተት

ከመቼውም ጊዜ በላይ በአገራችን ፖለቲካ ወጣት አመራሮችን በመያዝ የወጣቶች ፓርቲ የመሆን ውጥኑን አሳይቷል። ይህም ፖሊሲ የዚህ አንድ መገለጫ ሲሆን የአገራችን ዕደገት በወጣቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ይረጋገጣል የሚል አንድምታ አለው።

5. ዓላማ

የዚህ ፖሊሲ ዓላማ ወጣቶች የማህበረሰቡ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙ በመሆናቸው በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፍ ውስጥ እኩል/ፍትሃዊ ተጠቃሚ እና ትርጉም ባለው መልኩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በተመሳሳይ ወጣቶች አምራች እና አንቀሳቃሽ ሃይል ሆነው ለአገራችን ማበርከት የሚገባቸውን እንዲያበረክቱ አገራችንም የወጣቶች አስተዋፅዖ ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ ነው።በተጨማሪም የወጣቶች መብቶች የተከበሩባት፣ ሙሉ አቅምና ሃይላቸውን ተጠቅመው ለእድገቷ የሚሰሩላት፣ በዴሞክራሲ እና ልዩነቶች በንግግርና በሃሳብ ብቻ በመፍታት የሚያምኑ፣ እውቀትንና ቴክኖሎጂን የታጠቁ፣ የበረቱ ንቁ በስነምግባር የታነፁ አገርን የመረከብ ሃላፊነት የሚጣልባቸው ከዘረኝነት የራቁ ወጣቶች የሚኖሩባት ኢትዮጵያን መፍጠር የዚህ ፖሊሲ ዓላማ ነው።

6. መርህ

ይህ የኢትዮጵያ የወጣት ዜጎች የፖሊሲ ሰነድ የተዘጋጀው የወጣቱን የህበረተሰብ ክፍል ጥቅሙን ለማስጠበቅ እንዲሁም ወጣቱ እንደ ዜጋ በአገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ማበርከት ያለበትን አስተዋጽኦ ታሳቢ በማድረግ ነው። ፖሊሲው በገጠርና በከተማ ፤ አካል ጉዳተኞች እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶችን በሚኖሩበት አካባቢ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ፤ ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው እና ክብራቸው ተጠብቆ በአገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ንቁ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ፖሊሲው በመርህ ላይ በተደገፉ ቁልፍ የትግበራ ስትራቴጂዎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል። መርሆዎቹም ኃላፊነት፣ ተደራሽነት፣ ትርጉም ያለው ተሳትፎ፣ ቅንጅታዊ አሰራር፣ መደራጀት እና እኩልነት ናቸው።

- **ኃላፊነት፥** የመንግስት እና የግል ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ተቋማት ወጣቱ አቅሙን የሚያሳድግበትን፤ በመልካም ዕሴቶች የሚታነጽበትን ሁኔታዎችን መፍጠር አለባቸው።
- **ተደራሽነት፥** ወጣቱ በማህበራዊም ሆነ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ጉልህ እና ትርጉም ያለው የመሪነት ሚናን እንዲጫወት ጥራታቸውን በጠበቁ አገልግሎቶች ሊደገፍ፣ ሊበረታታ እና እኩልነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተደራሽ ሊሆኑለት ይገባል።
- **ትርጉም ያለው ተሳትፎ፥** ወጣቶች በሚኖሩባቸው አካባቢ እንዲሁም በአገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትርጉም ባለው መልኩ ተሳትፎ ሊኖራቸው ያስፈልጋል።
- **ቅንጅታዊ አሰራር፥** ሁሉም ባለድርሻ እና የሚመለከታቸው አካላት በትብብር ብሎም በቅንጅት ወጣቱ ተሰያውን፣ ችሎታውን፣ ብቃቱን፣ እውቀቱን እንዲሁም ተነሳሽነቱን በተሻለ መንገድ እንዲጠቀም በጋራ ሊሰሩ ይገባል።
- ***መደራጀት፥*** ወጣቶች የመደራጀትን አስፈላጊነት ተገንዝበው ሃላፊነት በተሞላበት መንፈስ መብታቸውን ለማስከበር፤ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን ለመገንባት እንዲደራጁ ዕድሎች እንዲሁም የህግ ማዕቀፎች ሊዘጋጁላቸው ያስፈልጋል።

- **እኩልነት፥** በፆታ፣ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ንቃተ-ሕሊና፣ እድሜ፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ የመኖርያ አካባቢ፣ አካላዊ እና አዕምሮአዊ ሁኔታን እና ሌሎች ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ወጣቶች መብታቸው እና ክብራቸው ተጠብቆ እኩል ዕድል (Equality of opportunity) እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል።

7. የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎች

7.1. የትምህርት ሥርዓትን ተደራሽ እና ጥራት ያለው ማድረግ

አምራች እና ተወዳዳሪ የወጣት ኃይልን ለመፍጠር ክህሎትን መሰረት ያደረገ ጥራት ያለው ትምህርት መሰረታዊው መሳርያ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የ2ተኛ ደረጃ እና የከፍተኛ ተቋማት ቁጥር አበረታች በሆነ ደረጃ ያደገ ቢሆንም የጥራት ደረጃቸው አሁንም ቢሆን እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።እንደ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ ልማት(United nation human development Index) ሀገራችን በትምህርት ጥራት ከ189 ሀገራት 173ተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ለትምህርት ስርዓቱ እንደ ዋነኛ ተግዳሮት የሚጠቀሱት የመምህራን ብቁ ሆኖ አለመገኘት ፣ የመማርያ አካባቢ ምቹ አለመሆን፣ የትምህርት በሚፈለገው ልክ ተደራሽ አለመሆን ፣ የትምህርት አሰጣጡ ክህሎት እና ተግባር ተኮር ያለመሆን፣ከመደበኛው የትምህርት አሰጣጥ በተጨማሪ የተለያዩ የአቅም ግንባታ እና የክህሎት ማጎልበቻ የስልጠና እድሎች አለመመቻቸት ፣የመሰረተ-ልማት ግንባታዎች አካል ጉዳተኞችን ያማከለ አለመሆን፣ የትምህርት ካሪኩለሞቹ ወጣቱ በዲሲፕሊን እና በአገር ፍቅርስሜት እንዲታነፅ ተደርገው አለመቀረፃቸው እና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህንና ሌሎችንም ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታትየሚከተሉት እንደ ፖሊሲ አቅጣጫ ተቀምጠዋል።

7.1.1. የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት

በገጠሪቷ የሀገራችን ክፍል የሚገኙ ወጣቶች አሁንም ቢሆን በአካባቢያቸው የትምህርት ተቋማት በቅርበት ስለማያገኙ ረጅም ርቀት ተጉዘው ለመማር ይገደዳሉ፡፡ ይህ በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ወጣቶች በቅርበት እንዲያገኙ ትኩረት ተሰጥቶ በብዛት የመገንባት ስራ ይሰራል። በተለይም የግሉ ሴክተር በስፋት በገጠሩ የሃገራችን ክፍል ትምህርት ቤቶችን እንዲገነባ አስቻይ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ።

እንደ አገር 36 የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና በርካታ የግል እንዲሁም የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና መስጫተቋማት ይገኛሉ። ነገር ግን እነዚህ ተቋማት የወጣቱን ፍላጎት እና ሽፋን ባማከለ መልኩ ተደራሽ አልሆኑም። በመሆኑም መንግስት ወደ ፊት በተጨማሪ ከሚያቋቁማቸው የትምህርት ተቋማት አልፎ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግሉ ሴክተር በብዛት ዘርፉን እንዲያሳድጉ ይደረጋል። የትምህርት ዘርፉን ለመደገፍ ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እና ለግሉ ሴክተር ከቀረጥ ነፃ አገልግሎት ጀምሮ የፋይናንስ እና የብድር አቅርቦት ይመቻቻል።

7.1.2 የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ

የትምህርት ስርዓት ጥራት አለው ከሚያስብሉት ነገሮች አንዱ እና ዋነኛው በጥልቀት እና አመክንዩ የሚያስቡ እና የሚመራመሩ ጠያቂ ወጣቶችን ማብቃት ሲቻል ነው። በዚህ ረገድ የአገራችን የትምህርት ስርዓት እጅግ ጎላ ቀርቷል። ስለሆነም የትምህርት ጥራቱን ለማማሻሻል ለወጣቱ በስነምግባር የታነፀ እና የትምህርት ደረጃው በሚጠይቀው ልክ ብቁ በሆኑ መምህራን ትምህርት ሊሰጠው ይገባል እንዲሁም የመማርያ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ በትኩረት ይሰራል። የመማርያ አካባቢዎች ንጹህ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ ብሎም ለሱሰ እና ለተለያዩ ጎጂ ልማዶች ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋሉ ይህ እንዲሆን አስፈላጊው ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፎች ይነደፋሉ ተግባራዊ ይደረጋሉ። በመደበኛም ሆነ በኢ-መደበኛ የትምህርት አሰጣጥ ልዩ ልዩ

የስልጠና እና የአቅም ግምባታ እድሎችን በማመቻቸት ወጣቱን በአለም አቀፍ ደረጃ የበለጠ ስኬታማ እና ተወዳዳሪ እንዲሆን ይታገዛል፡፡ የትምህርት አሰጣጡ ተግባር ተኮር እንዲሁም የስራ ገበያውን ያማከለ እንዲሆን ይደረጋል።

አብዛኛው የሀገራችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከጠቅላለ አመታዊ በጀታቸው 1% ብቻ የሚሆነውን ለጥናት እና ምርምር ያውላሉ። ይህ ዓይነት አካሄድ ወጣቱ ስራ ፈጣሪ እና ተመራማሪ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዳይሆን እየዳረገው ይገኛል። በመሆኑም ለጥናት እና ምርምር ዘርፉ የተሻለ በጀት እና በቴክኖሎጂ ታግዘ ወጣቱ ከአዳዲስ የምርምር ግኝቶቹ ላቅ ያለ ትሩፋት እንዲያገኝ ይደረጋል።

7.1.3. በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት አሰጣጥ

በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ወጣት ዜጎችን በብዛት ለማብቃት ከተፈለገ የትምህርት ስርዓቱ በእጅጉ በቴክኖሎጂ እና በአይ.ሲ.ቲ ሊደገፍ ይገባል። በተለይም የቴክኒክ እና ሙያ ፤ የምህንድስና እንዲሁም የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶችን ያለ ቴክኖሎጂ ድጋፍ ማሰብ አይቻልም። እንደ አብነትም በትምህርት ቤቶች የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት 29% ብቻ ነው ፤ ስለሆነም የኢንተርኔት አገልግሎትን ጨምሮ ዘመኑን የዋጁ ጥራት ያላቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ከአገር በቀል ዕውቀቶች ጋር በማጣጣም ለወጣቱ በስፋት ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

7.1.4. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወጣቶች

ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች፣ እና የአዕምሮ ውስንነት ችግር ላለባቸው ወጣት የህብረተሰብ ክፍሎች በልዩ ሁኔታ ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ በክህሎት እና በዕውቀት ማብቃት ያስፈልጋል። ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከሚቀላቀሉት ተማሪዎች ውስጥ 39% ገደማ እንዲሁም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከሚቀላቀሉት ውስጥ 37% ገደማ ብቻ የሚሆኑት ሴቶች ሆነው እናገኛለን። በመሆኑም በዋናነት በገጠሩ ሀገራችን አካባቢዎች ለሚማሩ ሴቶች የንፅህና መጠበቂያዎችን እና የመማርያ ቁሳቁሶችን የማሟላት እንዲሁም ማህበረሰቡ ስለሴት ልጅ የመማር አሉታዊ አስተሳሰቦችን የመቀየር ስራ ይሰራል።

በሀገራችነ ከ1% ያልበለጡ አካል-ጉዳተኞች ብቻ የትምህርት እድል ያገኛሉ። በመሆኑም አካል ጉዳተኛ ወጣት ተማሪዎችን ያማከለ መሰረተ-ልማት ብሎም በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ይመቻቻል። አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን ወላጆች እና አሳዳጊዎች በስፋት ወደ ት/ቤት እንዲልኩ የግንዛቤ ስራ ይሰራል። አካል-ጉዳተኛ እና ለጥቃት የተጋለጡ ወጣቶች ጥቃት እንዳይደርስባቸው በትምህርት ተቋማት አካባቢ ጠንካራ ህጋዊ ከለላ ይደረግላቸዋል።

የአእምሮ ውስንነት ላለባቸው ወጣት ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ በሰለጠኑ መምህራን ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ በክህሎት እና በእውቀት ብቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል።

7.1.5. የወጣት ክበባት እና ህብረቶች

በትምህርት ቤቶች ውስጥ መደራጀት እና በተለያዩ ዓይነት ክበባት ውስጥ መሳተፍ የአመራርነትን ጥበብ ለማዳበር፤ ተሰጥኦን ፈልጎ ለማግኘት ብሎም ተደራጅቶ መብትን ከማስከበር አንፃር አይነተኛ ሚናን ይጫወታሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ በሀገራችን በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የክበባት እና የተማሪዎች ህብረት እንቅስቃሴዎች የሉም ማለት በሚያስችል ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ስለሆነም እነዚህ የወጣቱን ማህበረሰብ ስብዕና የሚገነቡ አደረጃጀቶች በስፋት ከፖለቲካ እና ከሀይማኖት ጣልቃ ገብነት በፀዳ መልኩ እንዲደራጁ ይደረጋሉ ይበረታተሉ።

7.2. ጤናማ ወጣትን መፍጠር

ጤና ለወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል የሁሉ ነገር ምንጭ፣ መሰረተ እና አቅም ነው፡፡ ጤናው የተጠበቀ ወጣት በትምህርት እና ክህሎት ራሱን የሚያሳድግ፤ በአገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዘርፎች ላይ አዎንታዊ ሚናን መጫወት የሚችል ይሆናል፡፡ ተላላፊ የሆኑ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሀገራችን ወጣቱን እያጠቁ ያሉ የጤና ጠንቆች ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት፣ አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ፣ የአዕምሮ ህመሞች፣ ያልተፈለገ እረግዝና፣ ፆታዊ ጥቃቶች፣ ጎጂ ልማዶች፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሶች ጉድለት፣ ልቅ የሆነ የግብረ-ስጋ ግንኙነት እና የመሳሰሉት ወጣቱን ለጤናው መቃወስ አስተዋፅዖ እየዳረጉ የሚገኙ መንስዔዎች ናቸው፡፡

አብዛኛው ሰው ወሲባዊ ክንውኖችን የሚጀምረው የወጣትነት እድሜው ላይ ነው፡፡ 62 ፐርሰንት የሚደርሱ እድሜያቸው ከ25 እስከ 49 የሚደርሱ ሴቶች የመጀመሪያ የወሲብ ግንኙነታቸውን የሚያደርጉት ከ18 አመታቸው በፊት ነው፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ስለ ወሲብና ተያያዥ ጉዳዮች በቂ እውቀት ሳይኖራቸውና እራሳቸውን በወሲብ ከሚተላለፉ በሽታዎች ሳይጠብቁና እንዲሁም ዘመናዊ የወሊድ መከላከያ መንገዶችን ሳይጠቀሙ ነው፡፡ ከ10-24 ኣመት የእድሜ ክልል ላይ ያሉ ሴቶች የወሊድ መከላከያ አጠቃቀም ከ5 አመት በፊት ከነበረው 47.8 በመቶ ወደ 44.6 በመቶ ወርዷል፡፡ በተቃራኒው የአፍላ ወጣት ሴቶች እርግዝና ከነበረበት 3 በመቶ ወደ 8.6 አሻቅቧል፡፡ ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶችም በተገቢው መንገድ የማይስተናገዱና የኤችአይቪ ፕሮግራሞች ላይ በቂ የሆነ ትኩረት እየተሰጣቸው አይደለም፡፡

በዚህ የፖሊሲ ሰነድ ጤናማ ወጣትን ለመፍጠር መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ወጣቶች ለጤና እክል እንዳይጋለጡ የሚያደርጉ የመከላከል እርምጃዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። በዚህም መሰረት የዚህ ፖሊሲ ሰነድ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎች ወጣቶች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በማስቻል፣ ወጣቶች በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በስፋት እንዲሳተፉ ማስቻል ፣ የሥነ-ልቦና አገልግሎትን በስፋት ተደራሽ ማድረግ ፣ ጤናማ የወሲብ ግንኙነት እና የሥነ-ተዋልዶ እንዲኖር ማስቻል እና ለወጣቶች የተሟላ የጤና አገልግሎቶችን ማዳረስ ናቸው።

7.2.1. ወጣቶች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማስቻል

በአገራችን ካለው ድህነት እና ደካማ የአኗኗር ዘይቤ የተነሳ ወጣቶች የተመጣጠነ ምግብን የማያገኙ ሲሆን በዚህም አማካኝነት ወጣቶች የተመጣጠነ ምግብ ባለመመገባቸው ምክንያት ለአካላዊ እና ለሥነ-ልቦናዊ ችግሮች ይዳረጋሉ። ይህን ለማድረግ ወጣቶች የተመጣጠነ ምግብን የሚያገኙበትን ሁኔታዎች ጥናት ላይ መሰረት በማድረግ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

7.2.2. ወጣቶች በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በስፋት እንዲሳተፉ ማስቻል

በሌላ መልኩ ደግሚ የስፖርትዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የወጣቶችን አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጤንነት ሁኑኛ መፍትሄ ነው። ይህን ለማድረግ እንዲቻል ወጣቶችን በተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ አስቻይ የሆኑ ማዕቀፎችን በመንደፍ ምቹ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲሰሩና ወጣቶች በስፖርት እንቅስቃሴዎች በስፋት እንዲሳተፉ ይደረጋል።

7.2.3. የሥነ-ልቦና አገልግሎትን በስፋት ተደራሽ ማድረግ

በአገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ወጣቶች ለድብርት፣ ለጭንቀት እንዲሁም ለመሳሰሉ የሥነልቦና ችግሮች ተጋላጭ ለሚያደርጉ እንደትምህርት ማቋረጥ፣ ሥራ አጥነት፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ ተስፋ ማጣት እና የመሳሰሉት ማህበራዊ ቀውሶች ተንሰራፍተው ይገኛል። እነዚህ የሥነ-ልቦና ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት በቀላሉ ቀሪ ሊደረጉ የሚችሉ ሆነው ሳለ አስፈላጊው የሥነ-ልቦና አገልግሎት ባለመሟላታቸው ምክንያት ችግሮቹ ተባብሰው ይገኛሉ። ይህን ችግር ለመፍታት ሁሉም

ባለድርሻ አካላት በትብብር እና በቅንጅት ለመከላከል ሊሰሩ ይገባል።የማገገሚያ ማዕከላትን ለወጣቱ በተገቢው መልኩ ተደራሽ በማድረግ የሥነ-ልቦና አገልግሎቶች በሰለጠኑ ባለሙያሞች እንዲሰጡ ይደረጋል።

7.2.4. ጤናማ የሥነ-ተዋልዶ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል

ጠንካራ የሥነ-ተዋልዶ ጤና ስርዓት መኖር ወጣቶች ጤናማ የሆነ እንዲኖራቸው ብሎም የተስተካከለ የሥነ-ተዋልዶ ሥርዓት እንዲኖር ከማድረግ አኳያ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በኢትዮጵያ ባለፉት አመታት በወጣቶች ሥነ-ተዋልዶ ጤና ላይ የተዘጋጁ የፖሊሲ እና የስትራቴጂ ሰነዶች ያሉ ቢሆንም በዘርፉ የሚስተዋሉት ችግሮች ለመቅረፍ አልተቻለም። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሆኑት በሥነ-ተዋልዶ ጉዳዬች ላይ ያለው ከፍተኛ የግንዛቤ እጥረት እንዲሁም ከግንዛቤ እጥረት ተያይዘው የመጡ ጤናማ የሆነውን ሥርዓት የሚያዛቡ የተንሸዋረሩ ምልከታቻዎች ፣ የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች በስፋት እና በጥራት መዳረስ አለመቻላቸው እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ያካተተ የፖሊስ እና የስትራቴጂ ማዕቀፍ ጉድለቶች ናቸው። ይህ የፖሊሲ ሰነድ ወጣቶች ከሥነ-ተዋልዶ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ፣ የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በስፋት እና በጥራት ማዳረስን እና የሥነ-ተዋልዶ ጤናን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ባለድርሻ አካላት ባማከለ መልኩ እንዲሰሩ የትኩረት አቅጣጫ ያደርጋል።

የሥኑ-ተዋልዶ ጤና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ

በማህበረሰብ ውስጥ ባለው የሥነ-ተዋልዶ ጉዳዮችን መሸፋፋን እና የማይደፈሩ ርዕሶች የማድረግ ዝንባሌ የተነሳ አብዛኛው የአገራችን ወጣቶች የሚኖራቸው መረጃ ሳይንሳዊ ያልሆነና የተንሸዋረረ ነው። ይህም በመሆኑ ብዙ ወጣቶች ጤናማ ያልሆኑ ልቅ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ያደርጋሉ፣ ላልተፈለገ እርግዝና ይጋለጣሉ፣ ለHIV/Aids እና ሌሎች ተያያዥ አባላዘር በሽታዎች ተጠቂ ይሆናል፣ ተደጋጋሚነት ላለው የጽንስ ማቋረጥ ሂደት ውስጥ ይገባሉ፤ በዚህም ምክንያት ወጣቶች ለጭነቀት፣ ለሥነ-ልቦና መታዎክ እና ሌሎች አሉታዊ ኹነቶች ይጋለጣሉ። ይህን ለመከላከል ወጣቶች ሳይንሳዊ የሆነ ትክክለኛ የሥነ-ተዋልዶ ጤና መረጃ ሊደርሳቸው ይገባል። ወጣቶች በጉዳዩ ላይ በስፋት እውቀት እንዲኖራቸው እንዲሁም ከሥነ-ተዋልዶ ጋር ዝምድና ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚወስዱት ውሳኔ ሳይንሳዊ እንዲሆን ሰፊ የዕውቀት እና የክሂሎት ማዳበር ሥራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፣ ምሎዕ የሆነ የሥነ-ተዋልዶ መረጃዎች በጥራት እና በስፋት ለወጣቶች እንዲደርሱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች በስፋት እና በጥራት ማዳረስ

ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ ለወጣቶች ምቹ እና ተደራሽ ያልሆነ የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ወጣቶች አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ከሚዳርጉ ሁኔታዎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው። ይህን ለመቅረፍ የተሟላ እና ለወጣቶች ምቹ የሆኑ የሥነ-ተዋልዶ አገልግሎት አሰራር ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል።

7.3. ወጣቶች ተጋላጭ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች በመከላከል እና በማስወገድ መልካም ወጣቶችን መፍጠር

ወጣቶች በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ለአሉታዊ ሁኔታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ። በአገራችን ያለው እጅግ ለከፋ ድህነት መንስኤ የሆነው አነስተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ፣ ውስብስብ የማህበረሰባዊ ችግሮች እና ሌሎች ችግሮች ተደራርበው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን ተጋላጭነት ሰፊ አድርገውታል። ይህ የፖሊሲ ሰነድ በተለያየ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን ተጋላጭ የሚያደርጓቸውን ሁኔታዎች የሚቀረፍበትን ሁኔታ በጥናት ላይ በመመስረት አስፈላጊ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ መፍትሄ ለማምጣት የተዘጋጀ ነው። በማህበረሰባችን ውስጥ ወጣት ሴቶች፣ በወንጀል ድርጊት ተሳትፍው የሚገኙ ወጣት ታራሚዎች፣ አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ፣ በተለያዩ ሱሶች የተጠቁ ወጣቶች፣ በአርብቶ አደር እና በገጠር አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች፣ በጎዳና ላይ የሚገኙ ወጣቶች እና ሌሎች ወጣቶች ለተለያዩ አሉታዊ ሁኔታዎች ተጋላጭ የሚሆኑ ሲሆን እነዚህን

ተጋላጭነት የሚፈጥሩ እና የሚጨምሩ አሉታዊ ሁኔታዎች በጥናት በመለየት የተለያዩ መርሃ-ግብሮች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመለየት መፍትሄ መለየት ያስፈልጋል።

7.3.1. ሴት ወጣቶችን ተጋላጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ማስወገድ

በከተማ እና በገጠር የሚኖሩ ሴት ወጣቶችን ተጋላጭ የሚያደርጉ ዘርፈብዙ ችግሮች ያሉ ቢሆንም ጾታዊ ጥቃት፣ አስገድዶ መደፈር፣ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የእናቶች ሞት፣ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ጠለፋ፣ልቅ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት፣ ሴተኛ አዳሪዎች፣ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አለመሟላት እና የቤት ውስት ሥራ ጫና መብዛት ዋነኞቹ ናቸው። በአገራችን በተለያየ አካባቢ እና ሁኒታዎች የሚገኙ ወጣት ሴቶችን ተጋላጭ በማድረግ ላይ የሚገኙ እነዚህ እና የመሳሰሉትን አሉታዊ ሁኔታዎች ለማስወገድ አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማዕቀፍ፣ የበጀት፣ የተቋም ማሻሻይ ሥራዎችን ጥናትን ማዕከል ባደረገ እና ሴቶችን ባሳተፈ መልኩ የሚከናወን ይሆናል።

7.3.2. በወንጀል ድርጊት ተሳትፈው የሚገኙ ታራሚ ወጣቶች

በኢትዮጵያ ወጣት ታራሚዎችን በሚመለከት በሥራ ላይ ያሉ የህግ እና የተቋም አሰራሮች በወንጀል ድርጊት ተሳትፈው የሚገኙ ወጣቶችን ለማረም እና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ አስቻይ ሲሆኑ አይተዋልም። በፌደራል እና በክልል ድርጃ ወጣት ታራሚዎችን የሚያስተግዱ ተቋማት ከፋይናንስ፣ ከሠው ኃይል እና ከመሰረተ ልማት አኳያ እጅግ ደካማ መሆን በወንጀል ድርጊት ተሳትፈው የተገኙ ወጣቶችን የሚያርሙ ከመሆን ይልቅ ወጣቶችን ይባሱኑ ወደወንጀል ድርጊት የሚመሩ ሆኑዋል። ይህን ለመከላከል ወጣት ታራሚዎችን የሚመለከቱ የህግ እና የተቋም ማዕቀፎች ጥናት ላይ መሰረት ባደረገ መልኩ በማሻሻል በወንጀል ድርጊት የተገኙ ወጣቶች የሚታረሙበትና የሚያገግሙበት መርሃግብሮች በፌደራልና በክልል መዋቅሮች ይነደፉ፣ ተግባራዊ ይደርጋሉ።

7.3.3. አካል ጉዳተኛ ወጣቶች

በኢትዮጵያ አካልጉዳተኛ ወጣቶች የተለያዩ ተግዳሮቶች ይገጥሟቸውዋል። ምቹ የሆነ የመሰረተ-ልማት አለመሟላት ፣ የአካል ጉዳተኞች ትክክለኛ ቁጥር አለመታወቅ ፣ ለአካል ጉዳተኛነት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው አሉታዊ አመለካከት እና ሌሎችም ችግሮች ተደራርበው አካል ጉዳተኞ ወጣቶን በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ አርገዋቸዋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ ለአካል ጉዳተኛ ወጣቶች አስፈላጊ የሆነው ድጋፍ እና ክትትል የሚደረግላቸው ይሆናል።

7.3.4. በተለያዩ ሱሶች የተጠቁ ወጣቶች

በአገራችን የሚገኙ ወጣቶች በከፍተኛ ሁኔታ ከመቼውም ጊዜ በላይ ለሱስ ተጋላጭ ሆነዋል። መረጃዎችን እንደሚያሳዩት በሀገራችን 37 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች እና 43 በመቶ የሚሆኑ እድሜያቸው ከ15-19 የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች አልኮል የሚጠቀሙ ሲሆን ፣ 57 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ጫት እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን ይጠቀማሉ። በአገራችን በአሁኑ ወቅት በወጣቶች ላይ እየተስተዋለ ያለው የሱሰኛነት ሁኔታ መጠን፣ ስፋት እና መንስኤ በጥናት ካለመረጋገጡም በላይ ለሱስ ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች እንዲያገግሙና ወደ ትክክለኛው የህይወት መስመር እንዲመለሱ የሚያደርግ ሳይንሳዊ፣ የተቀናጀ እና የተሟላ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ብዙ ለሱስ የተጋለጡ ብዙ ወጣቶች በቀላሉ ሊያገግሙ እየቻሉ ለተወሳሰበ የጤንነት መታወክ እንዲሁም እራስን ማጥፋት ሲጋለጡ እየተስተዋል ይገኛል። ወጣቶችን ቅድሚያ ለሱስ እንዳይጋለጡ የሚያደርጉ ተከላካይ እርምጃዎች አለመወሰድ፣ ለሱስ ተጋልጠው የሚገኙ ወጣቶችን ደግሞ እንዲያገግሙ የሚያስችል ምሉዕ ማዕከፍ ባለመኖሩ ችግሩን አባብሰውታል። ይህን ለመፍታት የወጣቶችን ለሱስ ተጋላጭነት የሚከላከሉ እርምጃዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የመፍትሄ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ፤ተጋላጭ ሆነው የሚገኙ ወጣቶች የሚያገግሙባቸው የማገገሚያ ማዕከላት በስፋት እና በጥራት ተገንብተው ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

7.3.5. በአርብቶ አደር እና በገጠር አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች

በአርብቶ አደር እና በገጠር አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ባለመቻላቸው ምክንያት ሰፊ የተጋላጭነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ወጣቶች የትምህርት፣ የጤና እንዲሁም ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማስቻል የዚህ ፖሊሲ ሰነድ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

7.3.6. ለስደት ተጋላጭ የሆኑ እና ከስደት ተመላሽ ወጣቶች

ኢትዮጵያ የስደት ዋነኛ ምንጭ ከሆኑ አገሮች አንዷ ስትሆን፤ በተወሰነ ደረጃም በአፍሪካ ቀንድ ለሚሰደዱ መጓጓዣና መዳረሻ አገር ሆና ታገለግላለች፡፡ ከሌሎች የእድሜ ቡድኖች ሲነጻጸር፤ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል (በከተማም ሆነ በተለይ ደግሞ በገጠር ያሉ) የኢትዮጵያ ወጣቶች ለስደት ተጋላጭ ናቸው። ወጣቶችን ለተዛባ ፍልሰት (irregular migration) የሚገፋፉት ዋነኛ መንሴዎች ድህነት፣ የኢኮኖሚ ዕድል ማጣት፣ በውጭ የተሻለ የኢኮኖሚ ምልከታ፣ የቤተሰብ-ግፊት (የትዳር አጋር ግፊት)፣ በእኩዮች ተጽዕኖ፣ በትምህርት ተደራሽነት እጦት፣ ትምህርት ማቋረጥ፣ ግጭቶች፣ የመሬት እጥረት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ እና ስደትን በተመለከተ በደላሎች የሚባዛ የተሳሳተ መረጃ ናቸው። የዚህ የፖሊሲ ሰነድ የመጀመሪያው ትኩረት በጥናት ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎችን በመለየት እነዚህን ችግሮች በመፍታት ወጣቶች ከአገራቸው እንዳይሰደዱ አማራጭ የኢኮኖሚ እድል መፍጠር ነው። ይህንንም ለማሳካት የፌደራል እና የክልል መንግስታት ቁርጠኝነት ወሳኝ መሆኑን ይህ የፖሊሲ ሰነድ ያምናል።

ከኢትዮጵያ የሚወጡ ብዙ ወጣት ሕገወጥ ስደተኞች በተለያዩ ሕገወጥ መንገዶች ለሕይወት አስጊ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ለህጋዊ ፍልሰት (regular migration) የሚጠየቁት የማይመቹ እና ከባድ የህግ እና የአሰራር መስፈርቶች ናቸው። ከዚህ አንፃር የዚህ የፖሊሲ ሰነድ ሁለተኛው ትኩረት በሕጋዊ መንገድ ወደ ውጭ ሃገር ለሥራ ለሚሄዱ ወጣቶች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር መብቶቻቸው እንዲጠበቁ ማድረግ ነው።

ከስደት ተመላሽ ወጣቶች በመጓጓዣ እና በመዳረሻ ሀገራት ከባድ አደጋዎች እያጋጠሟቸው መሆኑን የተለያዩ ዘገባዎች እና ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ የፖሊሲ ሰነድ ወጣት ስደተኞች በሚጓዝዙባቸው እና በመዳረሻ አገራት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አደጋዎች ለመከላከል እና ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያለመ ነው። በተጨማሪም ወጣት ስደተኞች የሚፈልጓቸውን አፋጣኝ ፍላጎቶች በመፍታት ለወጣት ምቹ በሆነ ሁኔታ ወደ ኢትዮጲያ ተመልሰው እራሳቸውን መልሰው የሚያቋቁሙበትን እድል ለመፍጠር ያለመ ነው። ለዚህም ሲባል ይህ የፖሊሲ ሰነድ የመጓጓዣ ወጪ ሽፋን (ይህ ማለት ከመድረሻ አገር እስከ መነሻ ቦታ)፣ የስነልቦና፣ የማገገሚያ እና የቁሳቁስ ድጋፍ እንዲሁም ስደተኞች መልሶ የማቋቋም ድጋፍ ለመስጠት የሚያችሉ ሥራዎችን ላይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

7.4. የስፖርት ፣ መዝናኛ እና ባህል እንቅስቃሴዎች በማሳደግ ወጣቱን ተጠቃሚ ማድረግ

ኢዜማ ወጣቶች የስፖርት፣ መዝናኛ እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች መሰረቶች ናቸው ብሎ ያምናል። ይህ የፖሊሲ ሰነድ ወጣቶች በነዚህ ድርጊቶች በስፋት በመሳተፍ የስፖርት ፣ መዝናኛ እና ባህል እንቅስቃሴዎችን እንዲያሳድጉ እንዲሁም ከዚህ ዘርፍ ወጣቶች እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ ማዕቀፎችን በስፋት እንዲዘጋጁ እና ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚደረጉ ይሆናል።

7.4.1. ስፖርት

ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ለወጣቶች አዕምሮዓዊ፣ አካላዊ እንዲሁም ስሜታዊ ዕድገት፣ ምርታማነት እና ጤንነት ለመጨመር መሰረታዊ ናቸው። ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች አዎንታዊ የፉክክር መንፈስን፣ በህብረት መትጋትን፣ ብርታትን እና የመሳሰሉ ባህሎችን በማዳበር ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ሁለንተናዊ ዕድገት ውስጥ ግንባር ቀደም ሚናን ይጫወታሉ። ስፖርታዊ

ውድድሮች የሀገራችንን ገፅታ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የሚገነቡ ፤ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖን የሚያበራክቱ ፤ አገራዊ አንድነትን እና የአገር ፍቅር ስሜትን የሚፈጥሩ መሆናቸውም አያጠራጥርም። በአገራችን ወጣቶች ለስፖርት ከፍተኛ ፍላጎትና ዝንባሌ ያላቸው ቢሆንም የስፖርት ዘርፉ ላይ በትኩረት ባለመሰራቱ አማካኝነት ወጣቶች በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ሲሳተፉ እንዲሁም የስፖርት ዘርፉ በሌሎች አገራት እንደሚታየው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጥቅም ሲያስገኝ አይስተዋልም። ባለፉት አመታት በስፖርት ዘርፉ ላይ የተንሰራፋውን ሙስና፣ የአስተዳደር ችግር፣ የዕውቀት እና ልምድ ማነስ፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ፣ የመሰረተ-ልማት አለመሟላት፣ ዘርፉን ለማሳደግ እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የማበረታቻ ሥርዓት አለመኖር እና ሌሎችም ተጠቃሽ የሆኑ ዘርፉ ብዙ ምክንያቶች የተነሳ የስፖርት ዘርፉ ወደኃላ ሊቀር ችሏል።

እነዚህን ዘርፉ-ብዙ ችግሮች ታሳቢ በማድረግ ወጣቶች በስፖርቱ ዘርፍ በስፋት እንዲሳተፉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የስፖርታዊ እንቅስቃሴ ዘርፎችና መስኮች ሊሰፉ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን እንዲያሳድጉ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስፖርታዊ መሰረተ ልማቶች በቴክኖሎጂ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ተደግፈው በጥራት እንዲገነቡ እና እንዲስፋፉ ይደረጋል። ለግሉ ዘርፍ የተለያዩ አይነት ድጋፎች እና ማበረታቻዎች በማድረግ ስፖርቱን እንዲደግፍ እና ከስፖርት ዘርፍ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያረጋግጥ ይደረጋል። በተጨማሪም ስፖርቱ ከዘረኝነት፣ ከሙስና ፣ ከአድሏዊአመለካከቶች፣ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ተላቆ፤ በስፖርታዊ ጨዋነት ተቃኝቶ የአገር ፍቅር ስሜት በወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ እንዲሰርፅ አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል። በተጨማሪም የስፖርት አስተዳደር ሥርዓቱ ለስፖርቱ ቅርብ በሆኑ ብቃት ባላቸው አመራሮች ሊተዳደር ይገባል። አካል-ጉዳተኞችን እንዲሁም ሴቶችን ወደ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች በስፋት እንዲሳተፉ ሊበረታቱ፣ ሊታገዙ እና አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሊሟሉላቸው ይገባል። በአገራችን እጅግ ሰፊ አገር በቀል የሆኑ ባህላዊ ስፖርቶችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ወደ ውድድር ስፖርት አይነቶች በማሳደግ እና በሀገር ውስጥም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ ከስፖርቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ለወጣቱ ሊያረጋግጡ ያስፈልጋል።

7.4.2. መዝናኛ

ወጣቱ ውጤታማ እንዲሆንና የደከመ አዕምሮውን እንዲያሳርፍ ምቹ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የመዝናኛ ስፍራዎች ወሳኝ እና አስፈላጊ ናቸው። ወጣቱ ማህበራዊ ቀውስን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ቦታዎች የሚያርቁት የተሟሉ የመዝናኛ ማዕከላት እናፅዱ እና አረንጓዴ ስፍራዎች በስፋት እና በጥራት መኖር ሲሆን የግሉ ዘርፍ እንዲሁም ወጣቱ በዚህ መስክ ላይ በስፋት እንዲሳተፍ የተለያዩ አይነት ማበረታቻዎች ሊደገፍ ይገባል:: ምቹ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ እና ተደራሽ የሆኑ እንደሲኒማ እና ቲያትር ቤቶችን፣ የጨዋታ ማዕከላትን፣ መጽሐፍት- ቤቶችን (Library)፣ እና የመሳሰሉትን ለወጣቶች መዝናኛ የሆኑ ሥፍራዎችን በስፋት እና በጥራት በግሉ ዘርፍ መሪነት እንዲስፋፉ ይደረጋል። በተጨማሪም ተሰጥዖ ያላቸው ወጣቶች በተለያዩ የመዝናኛ ዘርፎች በመሳተፍ ተሰጥዖቸውን እንዲያሳድጉ፣ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የመዝናኛ ዘርፉንም እንዲያሳድጉ ሰፊ ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

7.4.3. ባህል

ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሄረሰቦች የሚኖሩባት ሀገር እንደመሆኗ መጠን የተለያዩ ዓይነት የቁሳዊ፣ ትውፊታዊ፣ መንፈሳዊ ባህሎች እና ዕሴቶች ያሏት አገር ነች። ይሁንና ለዘርፉ ከተሰጠው ትኩረት አንፃር በሚገባው ልክ ወጣቱ ተጠቃሚ መሆን አልቻለም። ባህል የአንድ ህዝብ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን ወጣቱ ባህሉን እንዲያውቅ፣ እንዲያስፋፋ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን እንዲያረጋግጥ ሊሰራ ይገባል። የባህል ብዝሃነትን እንደ ፀጋ በመጠቀም ወጣቱ አንዱ የአንዱን ባህል በመማር

ለአገር አንድነት፣ ማህራዊ ፍትህን ለማስፈን፣ ለዲሞክራሲያዊ እና ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣ በጋራ የሚገጥመውን ችግር ለማለፍ እነዲሁም ተፈጥሮዓዊ ሃብቶችን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ መጠቀም መቻል አለበት።

ምንም እንኳን መሻሻሎች ቢታዩም ጎጂ ልማዳዊ ባህሎች አሁን በምንገኝበት ወቅት በብዙ የአገራችን አካባቢዎች ለዜጎቻችን የስቃይ ምንጭ ሲሆኑ ይስተዋላል። በተለይ በገጠሩ የአገራችን አካባቢዎች በሚኖሩ ወጣት ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ላይ በስፋት ይስተዋላል ፤ ይህ ደግሞ ለከፍተኛ አካላዊ፣ አዕምሮዓዊ እና ስነ-ልቦናዊ ህመሞች ያጋልጣል። ስለሆነም የጎጂ ልማዳዊ ባህሎችን ለማጥፋት ህብረተሰባችንን ከማስተማር ጀምሮ ጎጂ ልማዶችን በሚፈፅሙ አካላት ላይ አስተማሪ የሆኑ ቅጣቶችን በመጣል መከላከል ይገባል።

7.5. የወጣቱን የአገር ፍቅር ስሜት እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማሳደግ

ወጣትነት ጊዜን፣ ጉልበትን፣ ክህሎትን እና ተነሳሽነትን አጣምሮ የያዘ የእድሜ ክልል እንደመሆኑ መጠን በአገር ፍቅር ስሜት ተገርቶ ለአገር አንድነት እና ዕድገት ግምባር ቀደም ሚናን መጫወት የሚችል የማህበረሰብ ክፍል ነው። ስለሆነም ወጣቱን በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፍ በማበረታታት እና በማገዝ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፎች ላይ አዎንታዊ ለውጦች እንዲያመጣ ማብቃት ያስፈልጋል።

ባለፉት ሶስት አስርት አመታት ከፌደሬሽን ሀገረ-መንግስት አደረጃጀት ጀምሮ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የፖለቲካዊ ዘርፎች ዘርን፣ ቋንቋን እና ሀይማኖትን መሰረት አድርገው የተደራጁ በመሆናቸው ሳቢያ ወጣቱ በሚፈለገው ልክ በአገር ፍቅር ስሜት መንፈስ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ዘርፎች ውስጥ ሲሳተፍ አይስተዋልም። እንዲያውም በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ወጣቱ የሃገርን አንድነት አደጋ ላይ በሚጥሉ፣ የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፈው በሚሰጡ ጉዳዮች ላይ ሲተባበር ተስተዉሏል፡፡ በመሆኑም በመልካም ዕሴቶች የታነፀ፣ ሃላፊነት የሚሰማው እና የአገር ፍቅር ስሜት ያለው ወጣት በብዛት እንዲፈጠር እንደ መፍትሄ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል።

7.5.1. የወጣቱን የበጎ ፍቃድ አገልጎልት ማጎልበት

ባለፉት አመታት ወጣቶች በተለያዩ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በስፋት የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል። ይህን ሥራ ማጠናከር አስፈላጊ ሲሆን ወጣቶችን በስፋት በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች እንዳይሳተፉ የሚያደረጉ የተለያዩ አሉታዊ ሁኔታዎችን ነበሩ። እነዚህም የተቀናጀ፣ ዘመናዊ እና በማዕከል የሚገኝ የበጎ-አድራጎት ፈላጊዎች የመረጃ ቋት አለመኖር፣ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማድረግ እንደማበረታቻ አለመታየቱ፣ በጎ አድራጎትን የሚያስተባብሩ ስብስቦች፣ ኔትወርኮች እና ተቋማት አስፈላጊው የሆነ ህጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶላቸው ወጣቶች በተለያዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፍ አለመደረጉ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው። እነዚህን ታሳቢ በማድረግ በጥናት ላይ ተመስርቶ በብሄራዊ አገልግሎት ስርዓት ውስጥ ለሚያልፉ ወጣቶች በተለዩ የስራ መስኮች እና የትምህርትም ሆነ ሌሎች ዕድሎች ላይ ቅድሚያ የሚሰጥበት፤ በመረጃ ቋት የተደገፈ አሰራር እንዲዘረጋ እና እንዲተገበር ይደረጋል።

7.5.2. የወጣቱን አገር ፍቅር ስሜት የማሳደግ ሥራዎችን መስራት

ከፌደሬሽን ሃገረ-መንግስት አደረጃጀት ጀምሮ ማህበረሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀቶች ከዘር፣ ቋንቋ እና አካባቢያዊነት ተላቀው ፤ ወጣቱ በነፃነት ዜግነትን መሰረት ያደረጉ የመደራጀት አስቻይ ዕድሎች ሊመቻቹለት ይገባል። ብሎም በተለያዩ የሐገራችን ክፍል ለሚገኙ ወጣቶች በጋራ የሀገር ጉዳዩች ላይ በባለቤትነት መንፈስ የሚሳተፉበት ሐገራዊ አንድነትን እና መግባባትን ለመፍጠር የሚያግዙ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነነቶችን በስፋት መፍጠር አስፈላጊ ነው።

ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ብሄራዊ አገልግሎትን በአገር አቀፍ ደረጃ ማስጀመር

በፈቃድ ላይ የተመሰረተ ብሔራዊ አገልግሎት ሲባል ወጣቱ በፍላጎቱ እና በፈቃዱ በተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ እንዲሁም የውትድርና ስልጠናዎችን በመውሰድ አካላዊ ጤንነቱን የሚያጎለብትበት፣ ሐገሩን የሚያውቅበት ፣ መንፈሳዊ እና ሞራላዊ እርካታን እንዲሁም ስነ-ልቦናዊ ማንነቱን የሚቀርጽበት መንገድ ነው። የብዙ ሀገራት ልምድ እንደሚያሳየው የውዴታ ብሄራዊ አገልግሎቶች፤ ወጣቱን በስነ-ምግባር ለማነፅ፣ የስራ ባህሉን ከፍ ለማድረግ ብሎም ለሀገሩ ፍቅር እንዲኖረው ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ይህ አይነት የአገልግሎት መርሃ-ግብር እንደ ሃገራዊ አቅጣጫ ተይዞ ስላልተሰራበት ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች ወጣቱ ተጋላጭነቱ እንዲጨምር አስተዋፅኦ አበርክቷል።

7.6. ወጣቶች ትርጉም ያለው ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል

የወጣቶችን ትርጉም ያለው የፖለቲካ ተሳትበፖለቲካው ዘርፍ ያለው የወጣቶች ተሳትፎ እጅጉኑ የተዳከመ መሆኑ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ያሳለፈቻቸው እጅግ አሳዛኝ እና ደም አፋሳሽ የሆኑ የፖለቲካ ታሪኮች በወቅቱ በነበሩ ወጣቶች የተዘወሩ ቢሆኑምም ተደረገው በነብሩም ሆኑ እየተደረጉ ባሉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚስተዋለው የወጣቱ የፖለቲካ ተሳትፎ በስሜት የተነዳ ፣ ኢ-ዴሞክራሲዊ የሆነ ፣ በጥቂት የፖለቲካ ልሂቃን የሚዘወር መሆኑን ነው። በነዚህም ምክንያቶች የተነሳ ወጣቶች ከፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እንዲርቁ ተሳትፏቸውም ትርጉም አልባ እንዲሆን ተደርጎ ቆይቷል።

ወጣቱ በተደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ቁልፍ ሚና የነበረው ቢሆንም በአገሪቱ በተደጋጋሚ የመጡ ለውጦች ወጣቱን በሚያደርጋቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችና ተሳትፎዎች አማካኝነት ጥቃት እና ሰለባ የመሆን አደጋ ውስጥ በመክተታቸው ወጣቱ “ፖለቲካን በሩቁ” ፣ “ፖለቲካና ኮረንቲ” ወደሚሉ አመለካከቶች ገብቶ ከፖለቲካው ለረዥም አመታትእንዲርቅ ተደርጓል።

ወጣቱ አገሩን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይቀይራሉ በሚል እምነት በተለያዩ ወቅቶች የተሳተፈባቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የታለመላቸውን ውጤቶች ከማምጣት ይልቅ አገሪቱን ከአንድ አምባገነናዊ ሥርዓት ወደ ሌላ አስከፊ አምባገነናዊ ሥርዓት ሲያቀባብል ቆይቷል። ይህ ሁኔታ ወጣቶችን በተመለከተ እጅጉኑ አስከፊ የሚሆነው በወጣቶች ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የመጡ የፖለቲካ ለውጦች መልሰው የአገሪቱን ወጣቶች አለማሳተፋቸው ሳያንስ ወጣቱን ዋነኛ የጥቃት ሰለባ ማድረጋቸው ነው።

ባለፉት አመታት በተደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ለመጣው ለውጥ አንዱ ገፊ ምክንያት በወጣቶች ተደርጎ የነበረው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ አስከፊውን ስርዓት ከማዳከም እና ለውጡን ዕውን ከማድረግ አኳያ ትልቅ ድርሻ ቢኖረውም ለዘመናት አፈናን ፣ ጥላቻን ፣ አለመተማመንን እና የፖለቲካ መስመር አሁንም ቢሆን ወጣቶችን መደበኛ ወደሆነው የፖለቲካ መስመር እንዳይገቡ ይልቁንም በኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች ወጣቶች እንዲጠለፉ አድርጓል። ስለሆነም ይህ የፖሊሲ ሰነድ ወጣቶች በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው አስቻይ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠርን ቅድሚያ በመስጠት። ወጣቶችን ከፖለቲካ ተሳትፎ የሚገድቡ ሁኔታዎችን በመለየትና በማስወገድ ወጣቱ ብቁ የትምህርት ፣ የክህሎት እና የተለያዩ አቅሞችን እንዲያጎለበትና በአገሪቱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖረው ይደረጋሉ። ወጣቶች በነፃነት የፖለቲካ ውይይቶችና ክርክሮችን እንዲያከናውኑ ሁኔታዎችን ይመቻቻሉ፣ ማበረታቻዎችም ይደረጋሉ። ፖሊሲው የወጣቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማረጋገጥ በወጣቱ ዘንድ ጥራት ያለው እና ከብዥታ ነፃ የሆነ የፖለቲካ አቋም እንዲኖር በወጣቱ መካከል ነፃ የሆኑ የፖለቲካ ውይይቶችና ክርክሮች አስፈላጊ መሆናቸውን ያምናል።

በመሆኑም ይህ ፖሊሲ በወጣቶች መካከል የሃሳብ ነፃነትን መሰረት ያደረጉ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብን የሚገነቡ ውይይቶች እንዲኖሩ አስፈላጊው የህግ፣ የተቋምና የማበረታቻ ማዕቀፎችን ይቀረፃሉ፣ ተግባራዊም ይደረጋሉ።

7.7. ወጣቶች ለሰብዓዊ መብቶች እና ለዴሞክራሲያዊ ማህበረብ ግንባታ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ማስቻል

ከሰብዓዊ መብቶች ጥበቃና ክለላ እንዲሁም ከዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አኳያ ወጣቶች ትልቅ ሚና አላቸው። ሆኖም ግን በተንሸዋረረው የትምህርት ፖሊሲ፣ በከረረው የወቅቱ ፖለቲካ እና ወጣቶችን በስፋት ባቀፈው ኢ-መደበኛ አደረጃጀት አማካኝነት ወጣቱ ሊያስጠብቅ የሚገባቸውን ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱ እያየ በቸልታ እንዲያልፍ ይባስ ብሎም በተደጋጋሚ ሰብዓዊ መብቶች ሲጥስ ተስተውሏል። መቻቻል፣ ትብብር እና ስምምነትን መሰረት ያደረገን ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ወጣቶች ድርሻቸውን መጫወት ሲገባቸው እራሳቸው በስሜት በሚነዳ ፣ ጤናማ ያልሆነ በአክራሪነት የተሞላ ፋክክር ውስጥ ገብተው ይስተዋላል። ስለሆነም የሰብዓዊ መብቶች አከባበርና አጠባበቅ እንዲሁም ከዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ግንባታ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ላይ ወጣቶች የሚስተዋሉ የግንዛቤ ዕጥረቶች በተለይም ወጣቶች ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትልቅ ሚና ቢኖራቸውም ወጣቶች ዘንድ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ወጣቶች መብቶችን ባልተገባ ሁኔታ ሲገድቡ ይስተዋላል። ወጣቱ ከዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ግንባታ ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊው ግንዛቤ እንዲኖረው እና የበኩሉን ሰፊ ድርሻ ሊያበረክት ይገባል። ስለሆነም ወጣቶች ለሰብዓዊ መብቶች መከበር እና ለዴሞክራሲ ማህበረሰብ ግንባታ ቁልፍ ሚና እንደሚጭእወቱ በማመን ወጣቶች የሰብዓዊ መብቶችን ላይ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ብሎም ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ዘብ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በስፋት ይሰራሉ።

7.8. የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

ሥራ አጥነት በከተሞች እንዲሁም በገጠርም የሚታይ ችግር ነው። ይህ የሥራ አጥነት ችግር ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን የሚያስከትል መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የወጣቶች ሥራ አጥነትን መቆጣጠር አለመቻል ወጣቶች በግራ መጋባት ውስጥ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህም ለተለይ ሱሶች ተጋላጭ እንዲሆኑ፣ በወንጀል ተግባራት እንዲሰማሩ እና አሁን እንደምንመለከተው የአክራሪ ብሔርተኞች መጠቀሚያ እንዲሆኑ እንዲሁም ለህገወጥ ስደት እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል። በመሆኑም ወጣቶች የራሳቸውን እና የቤተሰባቸውን ህይወት ለመቀየር ሥራ አግኝተው እንዲቀጠሩ አልያም የሥራ-ፈጣሪ እንዲሆኑ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል።

ባለፈው ሥርዓት የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በርካታ መፍትሄዎች በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ሲወሰዱ ነበር። ሆኖም ግን የተወሰዱት መፍትሄዎች በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ ከመሆናቸውም በላይ የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ሊመልስ በሚችል መልኩ የተነደፉ አልነበሩም። ይባስ ብሎም በተለያዩ ጊዜያት መንግስት የወሰዳቸው የሥራ ፈጠራ ዕርምጃዎች ወጣቶችን ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት የገነነባቸው፣ ለሙስና፣ ለአድሎአዊ እና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ ሲሆኑ ወጣቶችን ኢኮኖሚያዎ ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ ይባስ ተስፋ እንዲቆርጡ ሲገፋፉ ተስተውሏል።

7.8.1. ወጣቶች በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል

አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ ሀገራት ለእድገታቸው ትልቅ የሚባል አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። የነዚህ ተቋማት መጠንከር ለስራ ፈጠራ እና አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት መሰረታዊ የሚባል አስተዋጽኦን ያበረክታሉ። በአለም ባንክ ጥናት መሰረት እነዚህ ተቋማት የዓለምን የንግዱን ዘርፍ 90% እንዲሁም 50% የሚሆነውን የስራ ፈጠራ ዘርፉን እንደሚሸፍኑ ይገመታል። በሀገራችን ኢትዮጵያም እያደገ ያለውን የስራ ፈላጊ ወጣት ቁጥርን

ለመሸፈን በየዓመቱ ቢያንስ 2 ሚልየን ገደማ የሥራ ዕድሎች መፈጠር አለባቸው። ይህም እንዲሳከ ከተፈለገ በተለይ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይሶችን በብዛት መፍጠር እና መደገፍ ከፍተኛ ቅድሚያ እንዲሰጠው የግድ ይሆናል። ለዚህ ዘርፍ እንደማነቆ የሚነሱ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ውስጥ የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ችግር ፣ ደካማ እና ኋላ ቀር መሰረተ-ልማቶች ፣ አስቻይ እና አበረታች ያልሆኑ የህግ ማእቀፎች፣ ፍትሃዊ ያልሆነ የገበያ ውድድር ፣የአስተዳደር ክህሎት እጥረት ፣በሙስና የተዘፈቀ አሰራር እና የመልካም አስተዳደር እጥረት ፣ ብቸኛ የፋይናንስ ምንጮች ከቤተሰብ ወይም ከቁጠባ እና ከእቁብ የሚገኙ መሆናቸው እንዲሁም ግዙፍ የብድር የመያዣ መስፈርቶች እንደችግር ይጠቀሳሉ።

ከላይ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች ሀገራችን ከዘርፉ ሊገኙ የሚገቡ ጥቅሞችን እንዳታገኝ እያደረጉ ይገኛሉ። ይህ በመሆኑም በርካታ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ወጣቶች በስራ አጥነት እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ስለሆነም ከዘርፉ የበለጠ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማስመዝገብ የሚከተሉት እንደ ፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል። የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት በፋይናንስ እንዲጠነክሩ እና በቴክኖሎጂ እንዲበለፀጉ ይደረጋል። የብድር መሰረተ-ልማትን (የብድር ሪፖርት ስርዓቶችን ፣ደህንነቱ የተጠበቀ የግብይት ስርዓትን፣ የብድር ማስያዣ መመዝገቢያዎችን) በማስፋፋት እና በማሻሻል፤ ዘርፉ ያለበትን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ ይሰራል። ይህም የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት (MFI) ከብድር የዘለሉ አገልሎቶችን (noncredit service) እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለኢኮኖሚው የሚያበረክቱትን ሀያል አቅም አጉልቶ በማሳየት ብሎም የፋይናንስ ተቋማትን ተገቢ በሆነ አመራር እና እስትራቴጂ በማሻሻል የበለጠ ብቁ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ይደረጋል። ይህ የሚሆነነውም የተማረውን ወጣት የህብረተሰብ ክፍል ያገናዘበ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲሁም አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር ይሆናል። በተጨማሪም ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምቹ የንግድ ከባቢን (Ease of doing business) ለማሻሻል የህግ ማእቀፎች እና አሰራሮች ተዘርግተው ተግባራዊ ይደረጋሉ። ፈጠራን እና ቴክኖሎጂን ያማከለ ስርዓት በመዘርጋት ወጣት አዲስ ስራ ፈጣሪዎችን በፖሊሲ ትኩረት ተሰጥቷቸው ድጋፍ እና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል። ይህም የፈጠራ ክህሎትን እና የአስተዳደር ብቃትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የክህሎት እና አቅም ግንባታ ስልጠናዎች በወረዳ ደረጃ በመቅረፅ ተግባራዊ ይደረጋል። እንዲሁም መክሰር በራሱ የቢዝነስ አንድ አካል መሆኑን አምኖ፤ የታማኝነት መለኪያዎችን በማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በኩል በመንደፍ ኪሳራ ለሚያጋጠማቸው ታማኝ ወጣት ስራ ፈጣሪዎች ሁለተኛ እድል እንዲሰጥ አሰራር ተዘጋጅቶ ይተገበራል። የመንግስት እና የግል ተቋማት በዘርፉ ለሚደራጁ ወጣቶች የገበያ ትስስርን እንዲፈጥሩ ይደረጋል። እያንዳንዱ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የአረንጓዴ ልማትን እንዲያበረታቱ ብሎም ለዘርፎቹ አለም አቀፍ የገበያ ትስስርን እንዲፈጥሩ አስቻይ ሁኔታዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

7.8.2. ወጣቶች በመረጃና ግንኙነት ቴክኖሊጂ (Information and communication Technology) ዘርፍ በስፋት እና በጥራት እንዲሳተፉ ማስቻል

በምንኖርነበት በሉላዊነት (Globalization) ዘመን ወጣቶች በመረጃና ግንኙነት ቴክኖሊጂ ዘርፍ መረጃን በቀላሉ ለማስቀመጥ ለመለዋወጥ እንዲሁም ለአገር እድገት ብሎም በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የማእዘን ድንጋይ ሆኖ ያገለግላል። አለም በደረሰበት የስልጣኔ ደረጃ የሀገር ደህንነት ፣ የጤና ፣የግብርና፣ የፋይናንስ፣ የትምህርት ወዘተ የመሳሰሉትን ሴክተሮች ያለ መረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ ድጋፍ ማሰብ አይቻልም። በተለይ ለወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል ከስራ እድል ፈጠራ ጀምሮ የገበያ ትስስርን በመፍጠር ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አንጻር አይነተኛ ሚና ይኖረዋል። ይሁንና ከመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ ተደራሽነት ችግር እንዲሁም ጥራት ካላቸው የቴክኖሎጂ ስልጠናዎች እና የዳበረ ትምህርት ስርዓት እጦት ምክንያት በርካታ የአገራችን ወጣቶች ከዘርፉ መጠቀም በሚገባቸው ልክ መጠቀም አልቻሉም።

የኢትዮ-ቴሌኮም መረጃ እንደሚያሳየው በአገራችን ከ28 ሚሊየን በላይ የሚሆነው ህብረተሰብ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሲሆን ፣ 44.5 ሚሊየን የሚሆኑት ደግሞ የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ናቸው። ከዚህ ቁጥር ውስጥ 10 ሚልዮን ገደማ የሚሆነው የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ሲሆን ከዚህም ውስጥ አብዛኛው በወጣት የማህበራዊ ተጠቃሚዎች እንደሚያዝ ይገመታል። በአገራችን የሚገኙ ወጣቶች የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂን አጠቃቀም በጠቅላላው ስናየው ይህ የቴክኖሎጂ ዘርፍ ከማህበራዊ ሚዲያ ውጭ ባሉ ወጣቶችን በዕውቀት፣ በክህሎት እና በሥራ ፈጠራ ረገድ የሚረዱ ኹነቶች ላይ የአገራችን ወጣቶች ተጠቃሚነት አነስተኛ መሆኑን ነው። ይህ እንዲሆን ያደረጉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ቢኖሩም የኢንተርኔት ዋጋ ውድ፣ ጥራቱና ፍጥነቱ ዝቅተኛ መሆናቸው እንዲሁም በተደጋጋሚ የሚከሰቱ መቆራረጦች መኖርን ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም መንግስት ለዘርፉ ዕድገት የሰጠው ትኩረት በሕግና በማበረታቻ ሥርዓቶች ባለመደገፉ አማካኝነት ወጣቶች የላቀ ውጤት ሊያስመዘግቡ በሚችሉበት የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ጥቅም እንዳያገኙ ብሎም በስፋት በማህበራዊ ሚዲያዎች ብቻ እንዲወሰኑ አድርጓቸዋል። በመሆኑም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እኩይ ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ወጣቱ ለጥፋት ሲነሳሳ ተስተውሏል። እነዚህንና ዘርፈ ብዙ ማነቆዎች ለመፍታት እንደ ፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚከተሉት ተቀምጠዋል።

የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂን በጥራት እና በመጠነኛ ዋጋ ተደራሽ ማድረግ

በሀገራችን የአይ.ሲ.ቲ እና ኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ ይበል በሚያሰኝ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በሚፈለገው ልክ በተለይም በገጠራማው የሀገራችን ክፍል ተደራሽ ሊሆን አልቻለም፡፡ ስለሆነም የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት ፣ የአይ.ሲ.ቲ እና ኮሚዩኒኬሽን. መሰረተ ልማቶች ተጠናክረው በጥራት እና በመጠነኛ ዋጋ ለወጣቱ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል። በአይ.ሲ.ቲ ዘርፎች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት ምቹ እና በህግ ማዕቀፎች በተደፈገፉ አስቻይ ሁኔታዎች ጭምር በቅንጅት ወጣቱን ማህበረሰብ ክፍል ከዘርፉ ተጠቃሚነቱ እነዲረጋገጥ በጋራ ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል።

በየአካባቢ አስተዳደራት ዞኖች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጥራታቸውን የጠበቁ የአይ.ሲ.ቲ ፈጠራና ምርምር የልዕቀት ማዕከላት (Incubation centers) በዋናነት ወጣቱን ታሳቢ አድርገው እንዲቋቋሙ ይሰራል። በተጨማሪም ወጣቱ ከአይ.ሲ.ቲ. እና ኮሚኒኬሽን ዘርፎች ጋር በተያያዙ ጉዳየች ላይ የስራ ፈጠራ (Entrepreneurship) ፣ የአቅም ግንባታ እና ክህሎትን ማበልፀጊያ ስልጠናዎችን በቀላሉ የሚያገኝባቸው ሁኔታዎች የሚመቻቹለት ይሆናል።

ወጣቱን በመረጃና ግንኙነት ዘርፍ እንዳይሳተፍ ያደረጉ ማነቆዎችን ማስወገድ

ወጣቱ ወደ አይ.ሲ.ቲ ዘርፍ በስፋት እንዲቀላቀል የፈጠራ አእምሮአዊ ባለንብረትነት መብቱ ሳይሸራረፍ እንዲጠበቅለት ያስፈልጋል ብሎም የፋይናንስ አቅርቦት እና የገበያ ትስስርን በቀላሉ የሚያገኝበትን ስርዓት ሊመቻችለት ይገባል። ይህ ወጣቶችን በዘርፉ በስፋት እንዲሰሩ ብቻም ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ሁነኛ ሚና ይጫወታል። በተጨማሪም ከወዲሁ የሳይበር ደህንነትን የሚያረጋግጡ እና የሳይበር ጥቃትን የሚመክቱ ጠንካራ ተቋማት ሊገነቡ ያስፈልጋል፤ የተቋቋሙትንም ተቋማት እንዲጠናከሩ ትኩረት ተሰጥቶባቸው ይሰራል። በመጨረሻም ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እና ክትትል እየተደረገለት ከፈጠራ ውጤቶቹ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል።

ወጣቶችን በማህበራዊ ሚዲያ ከሚተላለፉ ሀሰተኛ እና እኩይ መረጃዎች መጠበቅ

ማህበራዊ ሚዲያዎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ቢኖሯውም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ለእኩይ ተግባራት መረጃዎች መለዋወጫ መሳርያነት ሲውሉ ይስተዋላል። በዚህም ወጣቶች በማህበራዊ ሚዲያ በሚደረጉ ሀሰተኛ መረጃዎች ተጠቂ ሆኗል። ይባስ ብሎም ወጣቶች ኢንተርኔትን ባልተገባ መንገድ በመጠቀም ራሳቸውንም አካባቢያቸውን ሲጎዱ ይስተዋላል። ስለሆነም ወጣቱ ሃሳቡን በነፃነት የመግለጽና መረጃን የማግኘት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበራዊ ሚዲያዎችንም ሆነ ሌሎች ድረ-ገፆችን

በሃላፊነት እንዲጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫዎች መስራት እና የተለያዩ ሁኔታዎችን በመጠቀም ወጣቱ እራሱን ለአላስፈላጊ አሉታዊ ትዕይንቶች እንዳያጋልጥ ጥበቃ ይደረግለታል።

7.8.3. የወጣቱ ከግብርናው ዘርፍ ያለውን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

የሀገራችን ከ80-85 በመቶ አካባቢ የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በገጠራማ አካባቢ ይኖራል ተብሎ ይገመታል። ይህ የህብረተሰብ ክፍል በዋናነት መተዳደርያው ግብርና ሲሆን የግብርናው ዘርፍ እንደ ሀገር 80 በመቶ አካባቢ ለሚሆኑ የሀገራችን ዜጎች የስራ እድልን በመፍጠር ፤ 90 በመቶ የሚሆነውን የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት፤ ከአመታዊ ጂ.ዲ.ፒ 50 በመቶውን በመያዝ ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት የጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለግላል። ኢትዮጵያችን ለግብርናው ዘርፍ በቂ እና አስተማማኝ የሆነ የውሃ ሀብት ፤ለም እና ሰፊ ያልታረሰ መሬት ፤ ለምርት ብዝሃነት የተመቹ የተለያዩ የአየር ንብረቶች ፤ በጉልበቱም በእውቀቱም ግብርናው ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ ተጠቃሚነቱን ሊያረጋግጥ የሚችል ወጣት የሰው ኃይል ቢኖራትም ዘርፈ ብዙ ከሆኑ ማነቆዎች የተነሳ በአጠቃላይ ሀገራችን በተለይም ደግሞ ወጣቶች በሚገባው ልክ መጠቀም አልቻሉም። በተለይ ከገንዘብ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት፤ ከተበጣጠሰ የውርስ መሬት፤ ከማደበርያ እጥረት ፤ ከገበያ ትስስር ፤ ተገቢ የግብርና ስልጠናዎች እና ድጋፎች ካለማግኘት ፤ ከመሰረተ-ልማት ተደራሽነት ፤ከምርጥ ዘር አቅርቦት እና የመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ ወጣቱ ከግብርናው ዘርፍ ማግኘት ያለበትን ጥቅም በእጅጉ የተዳከመ ነው።

በተጨማሪም ሀገራችን በተለያዩ የእንስሳት ልማት ሰፊ ሃብት ያላት ቢሆንም ይህ ዘርፍ እጅጉን ተዳክሞ ይገኛል። አገራችን በአሳ፣ በዶሮ፣ በከብት፣ በእንስሳት መኖ እንዲሁም በሌሎች ተያያዥ የግብርና ዘርፎች እምቅ አቅም ቢኖራትም ዘርፉ በመንግስት በሚገባው ልክ ትኩረት ካለማግኘቱ፤ ጠንካራ የሆነ የእንስሳ አርቢዎች ማህበር ካለመኖር፤ የእንስሳት አርቢዎች በቂ የሆነ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ካለመጠቀም እንዲሁም የእንስሳት እርባታ ስልጠናዎች እና የገበያ ትስስሮች በቀላሉ ካለመመቻቸት እና ከመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ ወጣቱ ተጠቃሚ መሆን ሳይችል ዘልቋል።

ከግብርና መሬት፣ መሰረተ-ልማት እና ከህሎት ጋር የተያያዙ ማነቆዎችን መቅረፍ

በገጠር የሚኖሩ ወጣቶች በአብዛኛው ከወላጆቻቸው ውርስ የሚያገኙት የተበጣጠሰ መሬት ምርታማነትን ስለሚቀነሰ መሬቶቹ ተጠንተው ወጣቶች በጋራ የሚያለሙበት መንገድ ማመቻቸው አስፈላጊ ነው። የምርት ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ የየአካባቢውን አየር ንብረት እና መልክ-አምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ያደረገ ጥልቅ ስትራቴጂካዊ ጥናት ተደረጎ ወጣቱን ከግብርና ዘርፉ ተጠቃሚነቱ ይረጋገጣል። ለምርት ማጓጓዝ ምቹ የሆነ የመሰረተ ልማት እና በአንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የገበያ ትስስር በመፍጠር ፣ የእንስሳት መኖ በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም የፀረ-አረም እና ምርጥ ዘር አቅርቦቶች በቀላሉ የሚያገኝበትን ስርዓት ተዘርግቶ ወጣቱ ከዘርፉ ተጠቃሚነቱ እንዲጎለብት ይሰራል።

በግብርና ላይ ለተሰማራው ወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል ጠንካራ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት በመሬቱ ላይ ውጤታማ ስራ እንዲሰራ የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኝ ይሆናል። እንዲሁም የግሉ ሴክተር እና ባለሀብቱ ወደ ግብርና ዘርፉ በስፋት ገብተው ለወጣቱ የስራ እድሎች እነዲፈጠር በህግ ማዕቀፉት እና በፖሊሲ ጭምር ትኩረት ተሰጥቶበት ይሰራል።

የአፈር እና ውሃ ጥበቃ እንዲሁም ዘመናዊ እና ውጤታማ የእርሻ አስተራረስ ዘዴ ከህሎቶችን ወጣቱ በቀላሉ የሚያገኝበትን መንገዶች እንዲመቻቹለት ይደረጋል። እንዲሁም ወጣቱን በስፋት የደን ልማት ስራዎች ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ ያስፈልጋል። ብሎም ለኮንስትራክሽን እና ለእንጨት ስራ ግብዓት የሚሆኑ ትርጉም ያለው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ የደን ምርቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሳተፍ የክትትል ፣ የድጋፍ እና ስልጠና እድሎች ይመቻቹለታል።

የእንስሳት እርባታ ላይ ወጣቶች እንዲሳተፉ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር

የእንስሳት እርባታ ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ ወጣቶች ከተመረጡ እና የተሻለ ምርትን ከሚሰጡ የእንስሳት ዝርያዎች አንስቶ ፣ የእንስሳት መኖ፣ የክትባት አገልግሎቶች፣ የገበያ ትስስሮች፣ የብድር እና የስልጠና እድሎች ይመቻቻሉ ብሎም በከተማ የእንስሳት እርባታ ግብርና ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ ወጣቶች እንደ መሬት አቅርቦት ካሉ ድጋፎች አንስቶ ዝርዝር አሰራር እና እስትራቴጂ ተቀርፆ አስቻይ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። በተጨማሪም ወጣቱ ዝናብን እየጠበቀ ከማረስ አልፎ አሳ ለማርባት የሚያስችለውን ሰፊ የመስኖ ልማት ስራዎች ሊገነቡ ይገባል። በተጨማሪም በየዘርፉ ጠንካራ የግብርና እንዲሁም የአሳ ማህበራት እና ዩኒየኖች እንዲመሰረቱ ይበረታታሉ ይደገፋሉ።

ወጣቱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲጠቀም በኪራይ መልክ ወይም በአነስተኛ ወለድ እና በረጅም የእፎይታ ጊዜ በሚከፈል የብድር አገልግሎት በማመቻቸት ምርት እና ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ማድረግ ይገባል፡፡ በአግሮ-ኢንደስትሪም ላይ በግልም ሆነ ተደራጅተው መሳተፍ ለሚፈልጉ ወጣቶች በልማት ባንክ በአፈፃፀም፣ በብድርም ሆነ የማምረቻ ቁሳቁሶች አቅርቦት ጊዜ ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመቅረፍ ወጣቱ ዘርፉን በስፋት እንዲቀላቀል ይሰራል፡፡

7. ኃላፊነት እና ተግባር

7.1. መንግስት

- የወጣቶችን ጉዳይ በዋናነት ጉዳዩ አድርጎ የሚሰራ እና የሚከታተል መንግስታዊ ተቋም እንዲኖር በማድረግ የወጣቶች ጉዳይ በብሄራዊ ደረጃ እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል።
- መንግስት የወጣቶችን ጉዳይ የመምራት፣ የማስተባበር፣ በሌሎች ዘርፎች በቂ ትኩረት እየተሰጠው መሆኑን የመከታተል እና የማረጋገጥ፣ የወጣቶችን አቅም የመገንባት እና ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊወን ሁሉ የማሟላት ኃላፊነት አለበት።
- የወጣቶችን ችግሮች ለመለየት እና መፍትሄ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን፣ መርሃ-ግብሮችን (Projects) ይነድፋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ ያስፈጽማል እንዲሁም ያስተባብራል። በተጨማሪም አለም አቀፍ እርዳታዎችን በማሰባሰብ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

7.2. ወጣቶች

- ራሳቸውን ማሳደግ እና ማበርታት፣ ለህጎች እና ደንቦች ተገዢ በመሆን መልካም ዜጋ መሆን።
- የሚከፈቱላቸውን እድሎች እና አጋጣሚዎች በአግባቡ መጠቀም።
- አገራቸውን የሚጠቅሙባቸውን በርካታ ተግባራት ማከናወን።
- ለወጣቶች ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር በግል እና በመደራጀት አብሮ የመሥራት ኃላፊነቶች አሉባቸው።

7.3. መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት (አለም አቀፍ እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች)

- በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎች ወጣቶችን የሚጠቅሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና በሥራዎቻቸውም ወጣቶችን አካታች መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- የተሻሉ ዕርዳታዎችን ወጣቶችን ለሚጠቅሙ ተግባራት ማዋል።
- ይህ ፖሊሲ በሚረቀቅበት እና በሚፀድቅበት ጊዜ ያልታዩ ጉዳዮችን መፍትሄዎችን እና ስትራቴጂዎችን እንዲጠኑ፣ እና በሚከለሱም ጊዜ ባለድርሻነትን ሚና መውሰድ።

7.4. ቤተሰብ

- መልካምነትን የተሞሉ ወጣቶችን ለማፍራት የቤተሰብን መልካምነት በማረጋገጥ ፣ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሥራት መልካም ወጣቶችን ማፍራት።

7.5. የሃይማኖት ተቋማት

- ወጣቶች እንደየሃማኖት ተቋም ተከታይነታቸው ለሃገራቸው ሊያበረክቱት ስለሚገባቸው አስተዋፅአ እና ማሳየት ስለሚገባቸው የመልካም ዜጋ ስነምግባር የመምከር፣ የመገሰፅ እና የማነፅ ሓላፊነት አለባቸው።።

8. አባሪ